በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚ ችሎት

የሰ.መ.ቁ 217195
ግንቦት 30 ቀን 2014 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** እትመት አሠፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- ወ/ሮ ፍርነስ ፈንቴ -- አልቀረቡም

ተጠሪ፡- የደብረማዊ ንዑስ ማዘጋጃ ቤት -- አልቀረቡም

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ ነው፡፡ በመሆኑም መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍርድ

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካች ሕዳር 17 ቀን 2014 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 03-102586 ሐምሌ 09 ቀን 2013 ዓ.ም በዋለው ችሎት የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ በመሻር ጉዳዩን የማየት የሥረ -ነገር ስልጣን የላቸውም በሚል ሲል የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

ጉዳየ የሥረ-ነገር ስልጣን ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁን አመልካች በቀን ሕዳር 18 ቀን 2013 ዓ.ም በተጻፈ የክስ አቤቱታ በይልማና ዴንሳ ወረዳ ፍ/ቤት በተጠሪ ላይ ባቀረቡት ክስ የነበራቸውን መሬት ለአመልካችና ለልጆቻቸው የቤት መስሪያ ቦታ ሳይሰጥና በቀሪው ይዞታ ላይ ካሳ ሳይከፈላቸው ተጠሪ ይዞታውን ለሌሎች ግለሰቦች የሰጠባቸው በመሆኑ ለአመልካችና ለልጆቻቸው የቤት መስሪያ እንዲሰጣቸው፣ በቀሪው ይዞታ ደግሞ ተገቢው ካሳ እንዲከፈላቸው ዳኝነት በመጠየቃቸው ነው፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ተጠሪ ታሕሳስ 5/2013 ዓ.ም በተጻፈ መልስ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያና በፍሬ ነገር መልስ ያቀረበ ሲሆን ይዘቱም አመልካች የካሳ ጥያቄ የሚያቀርቡት በአስተዳደራዊ መንገድ ሆኖ በይግባኝ በከፍተኛ ፍ/ቤት መቅረብ ያለበት መሆኑን፣ ሰበር ሰሚው  ፍ/ቤት ክስ እንዲያቀርቡ የወሰነላቸው የቦታ ጥያቄ እንጅ የካሳ ጉዳይ ጭምር አለመሆኑን፣ ለአመልካች እና ለ1ኛ ልጃቸው 750 ካ.ሜ ቦታ የተሰጣቸው መሆኑን፣ ሌሎቹ ልጆች ግን  መስፈርቱን የማያሟሉ መሆኑን፣ ቀሪውን ይዞታ ተጠሪ የማይፈልገው መሆኑን በመግለጽ መልሱን አቅርቧል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ፍ/ቤትም የግራቀኙን ምስክሮች በማቅረብ የሰማ ሲሆን አመልካች 500 ካ.ሜ፣ 1ኛው የአመልካች ልጅ 250 ካ.ሜ ይዞታ ያገኙ መሆኑን ቀሪ ልጆች መመሪያ ቁጥር 26/2008 ን መስፈርት ማለትም በወቅቱ ከአመልካች ጋር በስፍራው የማይኖሩ በመሆኑ ምክንያት መሬት ያልተሰጣቸው መሆኑን የቀረበው ማስረጃ ያስረዳል በሚል አመልካች ያቀረቡትን አቤቱታ ያልተቀበለው ሲሆን፣ ካሳን በተመለከተ አመልካች ካሳ ያልወሰደች መሆኑ በተጠሪ የታመነና ተጠሪ ትውሰድ በማለት በችሎት የገለጸ በመሆኑ ተጠሪ ለህዝብ አገልግሎት እንዲውል ከወሰደው መሬት ተመጣጣኝ ካሳ ለአመልካች እንዲሰጥ በሚል ወስኗል፡፡

በአመልካች በኩል ይግባኙ የቀረበለት የባህርዳርና አካባቢዋ ከፍተኛ ፍ/ቤት የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ በትዕዛዝ ያጸናው ሲሆን የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በበኩሉ የግራቀኙን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ ለህዝብ ጥቅም ለማዋል በሚወሰድ ንብረት አስመልክቶ የማከራከር የሥረ-ነገር ሥልጣን ያለው ከፍተኛ ፍ/ቤት ስለመሆኑ ከፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 15/2/ሠ/ ድንጋጌ ለመገንዘብ የሚቻል በመሆኑ የቀረበውን ክርክር የወረዳው ፍ/ቤት የማከራከር የሥረ-ነገር ሥልጣን ሳይኖረው መወሰኑና ከፍተኛው ፍ/ቤት በይግባኝ ማረም ሲገባው ይግባኙን መሰረዙ መሰረታዊ የሕግ ስሕተት ነው በማለት የአመልካችን ሥልጣን ባለው አካል ክስ የማቅረብ መብቷን ጠብቆ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንን ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡ አመልካች ሕዳር 17 ቀን 2014 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ በስር ፍ/ቤቶች ትእዛዝ ላይ ተፈፅሟል ያሉትን መሰረታዊ የሕግ ስሕተት ጠቅሰው በዚህ ችሎት እንዲታረምላቸው ጠይቀዋል፡፡ ፍሬ ቃሉም የስር ወረዳ ፍ/ቤት ተጠሪ ካሳ እንዲከፍል በሰጠው ውሳኔ ላይ ክርክር ባልተነሳበት ሁኔታ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አመልካች ይግባኝ ባሉበት መዝገብ አመልካችን በሚጎዳ መልኩ የወረዳውን ፍ/ቤት ውሳኔ መሻሩ ተገቢ አይደለም፣ ለህዝብ ጥቅም ሲባል የገጠር መሬት የሚነሳባቸው አርሶ አደሮች ቦታ አሰጣጥና ካሳ አከፋፈል መመሪያ ቁጥር 7/2010 አንቀጽ 36 እና የተሻሻለው መመሪያ ቁጥር 44/2013 አንቀጽ 60 ላይ በተጠቀሰው የቅሬታ አቀራረብ ሥርዓት መሰረት አመልካች ጉዳዩን ወደ ወረዳ ፍ/ቤት ያቀረቡበት አግባብ ተገቢ ሆኖ ሳለ የስር የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ከጉዳዩ ጋር ግንኙነት የሌለውን የፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 15 በመጥቀስ ውሳኔ መስጠቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ አመልካች ለጠየቁት ዳኝነት የወረዳ ፍ/ቤት የሥረ-ነገር ሥልጣን የለውም የመባሉን አግባብ አርሶ አደር ካሳ አከፋፈል እና ቦታ አሰጣጥ መመሪያ ቁጥር 7/2010 እና

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

የተሻሻለው መመሪያ ቁጥር 44/2013 አንጻር ለማጣራት ለዚህ ሰበር ችሎት ቀርቦ እንዲታይ በመታዘዙ ግራ ቀኙ የፅሁፍ ክርክር እንዲለዋወጡ ተደርጓል፡፡

ተጠሪ በቀን መጋቢት 22/2014 ዓ.ም በተጻፈ መልስ አመልካች ጉዳዩን ለስር ወረዳ ፍ/ቤት ያቀረቡት መመሪያ ቁጥር 7/2010 ም ሆነ 44/2013 ከመውጣቱ በፊት በመሆኑ የስር ፍ/ቤቶች በወቅቱ በነበረው መመሪያ ቁጥር 26/2008 እና በአዋጅ ቁጥር 455/1997 አንቀጽ 11 እንዲሁም በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 15 ላይ የተቀመጠውን ድንጋጌዎች መሰረት በማድረግ ውሳኔ የሰጡ መሆኑን፣ የክልሉ ሰበር ችሎት አመልካች አግባብ ባለው አካል መብታቸውን የመጠየቅ መብት አላቸው በማለት ወሰነ እንጅ አመልጃች ያቀረቡትን መብት በመመርምር ያሳጣቸው መብትም ሆነ የተጣለባቸው ግዴታ የሌለ በመሆኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት አለ ሊባል የማይችል መሆኑን በመግለጽ መልሱን አቅርቧል፡፡

አመልካች በበኩላቸው ከተጠሪ በቀረበው መልስ ላይ ሚያዚያ 13 ቀን 2014 ዓ.ም በተጻፈ የመልስ መልስ አመልካች ያቀረቡት የካሳ አነሰኝ ጉዳይ ሳይሆን ለአመልካችና ለ3 ልጆቻቸው ትክ መሬት ሊሰጣቸው እንደሚገባ በመግለጽ ዳኝነት የጠየቁ በመሆኑ የሥር ወረዳ ፍ/ቤት የሥረ-ነገር ስልጣነ አለው በማለት ቀድመው ያቀረቡትን መከራከሪያ በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

የግራቀኙ ክርክር እና በየደረጃው ባሉ ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ ይህ ችሎትም በሰበር አጣሪው ችሎት ሊጣራ ይገባዋል ተብሎ የተያዘውን ነጥብ ከግራቀኙ ክርክር፤ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

አመልካች በስር ፍርድ ቤት ካቀረቡት ክስ ይዘት በግልጽ መገንዘብ የቻልነው ሕጋዊ መብታቸው ሳይጠበቅ የገጠር መሬታቸው የተወሰደባቸው መሆኑን በመግለጽ መብታቸው እንዲጠበቅ ክስ ያቀረቡ መሆኑን ነው፡፡ ይህም አመልካች በገጠር መሬት ላይ ያላቸውን የይዞታ እና የመጠቀም መብት መሠረት በማድረግ ክስ ያቀረቡ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡

ከአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የገጠር መሬት አስተዳዳደር እና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 252/2009 አንቀጽ 52/2 ድንጋጌ ይዘት በግልጽ መገንዘብ እንደሚቻለው የወረዳው ፍርድ ቤት በገጠር መሬት ይዞታ እና የመጠቀም መብት ላይ የሚፈጠሩ አለመግባባቶችን እና የሚነሱ ክርክሮችን ተቀብሎ የማየት የስረ ነገር ስልጣን አለው፡፡

በያዝነው ጉዳይ አመልካች ክስ ያቀረቡት በገጠር መሬት ላይ ያላቸውን የይዞታ እና የመጠቀም መብት መሠረት በማድረግ በመሆኑ ከላይ በተገለጸው የአዋጁ ድንጋጌ መሠረት የወረዳው ፍርድ ቤት ጉዳዩን አከራክሮ የመወሰን የስረ ነገር ስልጣን አለው፡፡ ስለሆነም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን በዚህ አግባብ ተመልክቶ የፍሬነገር ክርክሩን መርምሮ መወሰን ሲገባው ከጉዳዩ ጋር ተያያዥነት የሌለውን የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 15/2/ሠ/ ድንጋጌን በመጥቀስ የወረዳው ፍ/ቤት የማከራከር የሥረ-ነገር ሥልጣን

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

የለውም በማለት የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ውሳኔ

1. በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 03-102586 ሐምሌ 09 ቀን 2013 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1 መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በውሳኔ የዘጋውን መዝገብ በማንቀሳቀስ የግራቀኙን ክርክር በስር ፍርድ ቤቶች ከተሰጠው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ መርምሮ ተገቢ ነው ያለውን ውሳኔ እንዲሰጥበት በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 341/1 መሠረት ጉዳዩ ተመልሶለታል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪ ግራቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡
   - መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ

አ/መ                                        የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ወሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም